ዝክረ ዐበይት ነቢያት

ነቢዩ ሕዝቅኤል

ታኅሳስ 2015 ዓ.ም





ይዘት

1 የስሙ ትርጉምና ትውልዱ

2 ለነቢይነት ስለመጠራቱ

3 ትንቢትና አገልግሎቱ

4 እረፍቱ

የስሙ ትርጉም ፡ ትውልድ

ሕ ዝ ቅ ኤ ል


‹ጽኑዕ ፤ ጽንዐ ኣምላክ›
‹ እግዚአብሔር ብርታትን ይሰጣል! ›

በነቢይነት የተላከው በዘመኑ ወደ ነበሩ ዓመፀኞች ሰዎች ስለ ነበረ እግዚአብሔር ብርታትን እንደሚሰጠው ያስረዳል

- የተወለደው በ623 ቅ.ል.ክ ነው።
- ነገዱ ከሌዊ ትውልዱ ከአሮን ነው።
- አባቱ ካህኑ ቡዝ እናቱ ደግሞ ህሪ ይባላሉ።
- ከልጅነቱ ጀምሮ የነቢዩ ኤርምያስ ደቀመዝሙር ነበር።
- የእስራኤል ካህን እና ባልትዳርም ነበር።

ስለነቢይነት ስለመጠራቱ

- ወጣቱ ነቢይና ካህን ሕዝቅኤል በ25 ዓመቱ ላይመለስ ኢየሩሳሌምን ትቷት ወደ ባዕድ አገር ኼዷል
- ከተማረኩት ወገኖቹ ጋር በኮቦር ወንዝ አጠገብ ይኖር ነበር
- በመጀመሪያዎቹ የምርኮ ዓመታት ነቢዩ የወገኖቹን ኹኔታ እያየ በአርምሞ ያለቅስ ነበር
- በተማረኩ በ5ኛው ዓመት ማለትም በ592 ከቅ.ል.ክ. አከባቢ ሰማያት ተከፈቱ።
- ሕዝቅኤል ራዕዩን ማየት የጀመረው በ30 ዓመቱ ላይ ነው።
- በዚኹ የትንቢት መንፈስ እየተመራም ለ22 ዓመታት ማለትም እስከ 570 ከቅ.ል.ክ. ድረስ እያገለገለ ቆይቷል።



ሕዝቅኤል ከምርኮ በፊት

01 ዘመኑ

- ንጉሥ ኢዮስያስ ባዕድ አምልኮን ለማስወገድ ፣ የእግዚአብሔርን ቤትና አምልኮ ለማሳደስ ይጣደፍበት የነበረበት ሰዓት ነበር
- ነቢያት ያንሰራሩበት ወራት ነበር
- የነቢዩ ኤርምያስን ለህዝቡ ያለውን ተግሳጽ ይሰማ ነበር

02 ወገኖቹ

- ጣዖታት በኢየሩሳሌም ጐዳናዎች ይታዩ ነበር
- የካህናቱና የመምህራኑ ሕይወት በክፋት የተለወሰ ነበር
- የቤተመቅደስ አገልግሎት የታጎለበት

03 ፖለቲካ

- የአሦር ዋና ከተማ የነበረችው ነነዌ ከመንግሥቷ ጋር ወድቃለች
- የግብጹ ንጉሥ የሚያገኘው የወርቅና የብር ግብር እንዳይቀርበት ኢየሩሳሌምን ሊያፈርሳት አለመውደዱ

04 ምርኮ

- የባቢሎኑ ንጉሥ ናቡከደነፆር የግብጹን ፈርዖን ኒካዑን ድል አደረገ
- የእስራኤል ንጉሥ ሰሎሞን በእግዚአብሔር መቅደስ ያኖራቸውን ንዋያተ ቅዱሳት ኹሉ ተማርከዋል
- የባቢሎኑ ንጉሥ ናቡከደነፆር ኢየሩሳሌምን ኹሉ ከድኾችና ከአገሩ ሕዝብ በቀር አሥር ሺህ ምርኮኞች አፍልሷቸዋል፡

ሕዝቅኤል በኮቦር ወንዝ

“በሠላሳኛው ዓመት በአራተኛው ወር ከወሩም በአምስተኛው ቀን በኮቦር ወንዝ በምርኮኞች መካከል ሳለሁ ሰማያት ተከፈቱ ÷ የእግዚአብሔርንም ራእይ አየሁ። ንጉሡ ዮአኪን በተማረከ በአምስተኛው ዓመት ከወሩም በአምስተኛው ቀን የእግዚአብሔር ቃል በከለዳውያን አገር በኮቦር ወንዝ ወደ ቡዝ ልጅ ወደ ካህኑ ወደ ሕዝቅኤል መጣ። የእግዚአብሔርም እጅ በዚያ በእኔ ላይ ሆነች።”

— ትንቢተ ሕዝቅኤል 1÷3



ትንቢተ ሕዝቅኤል

01 ከኢየሩሳሌም ውድቀት በፊት ስለ እግዚአብሔር ፍርድ

ምዕ.1-24

02 በአሕዛብ መንግሥታት ላይ

ምዕ.25-32


03 ከኢየሩሳሌም ውድቀት በኋላ ስለ እስራኤል መመለስ

ምዕ.33-48

ምዕራፍ 24



የአገልግሎቱ ይዘትና ሕይወቱ



ከኢየሩሳሌም ውድቀት በፊትና በኋላ

“ኢየሩሳሌም ልትወድቅ አትችልም” የሚል አጉል እምነት ነበራቸውና ከተማይቱ ከወደቀች በኋላ ግን የሕዝቡ መንፈስ ተለወጠና በኾነው ነገር እያዘኑ ተስፋ ስለቈረጡ

- በጐኑ በመተኛት
- የሚያረክሰውን በመብላት
- ጠጕሩን ቈርጦ በመበተን፣
- ዲዳ በመኾን
- ሚስቱ ስትሞት ባለማልቀስ
- በሌላም በአዲስ ኹኔታ እየታዘዘ ያስተምር ነበር

ይህም ሁሉ ቃሉን ይሰሙት ዘንድ ነበር!

ትንቢቶቹ

1

እግዚአብሔር በምሕረቱ ሕዝቡን እንደሚያድንና ለሕዝቡ ደንታ በሌላቸው እረኞች ላይም ፍርዱን እንደሚያመጣና በእነርሱ ፈንታም እርሱ ራሱ እረኛ እንደሚኾንላቸው

2

ወደ ምርኮ የኼዱት ኹለቱም ወገኖች ማለትም እስራኤልና ይሁዳ ተመልሰው አንድ እንደሚኾኑና ዳዊት ንጉሥ እንደሚኾንላቸው

3

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከከበረች ድንግል እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እንደሚወለድና ከወለድችውም በኋላ በድንግልና ፀንታ እንደምትኖር

4

ይኸን አዲስ ኹኔታ በአዲስ ቤተ መቅደስ ምሳሌነት ገለጠላቸው

ነቢዩ ሕዝቅኤል

ካኅን





ነቢይ

ባለ ራዕይ





የንስሓ አባት

የሥነ-መለኮት ምሁር



እረኛ




ጸሐፊ



እረፍቱ

ሚያዝያ 5 ስንክሳር



ያረፈው በሰማዕትነት ነው!

“የእስራኤል ልጆች በባቢሎን ሳሉ ጣዖት ባመለኩ ጊዜ ገሠፃቸው ፤ ስለዚኽም

አለቆቻቸው በላዩ አስነሥተው ገደሉት”

ምን እንማር?



የነቢዩ ኤርምያስ ደቀመዝሙር ነበር!

"ኃጢአተኛውም ከኃጢአቱ ተመልሶ ፍርድንና ቅን ነገርን ቢያደርግ በሕይወት ይኖርበታል።"

— ሕዝቅኤል 33÷19

"ሰውንም ባያስጨንቅ መያዣውን ባይወስድ ባይቀማም ከእንጀራውም ለተራበ ቢሰጥ ለተራቈተውም ልብስን ቢያለብስ÷እጁንም ድሀን ከመበደል ቢመልስ አራጣን ትርፎቻንም ባይወስድ ፍርዴንም ቢያደርግ በትእዛዜም ቢሄድ÷ እርሱ ፈጽሞ በሕይወት ይኖራል እንጂ በአባቱ ኃጢአት አይሞትም።"

— ሕዝቅኤል 18÷15



“እግዚአብሔርም ፦ ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም ÷ ሰውም አይገባበትም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ÷ ተዘግቶ ይኖራል።”

ትን.ሕዝ. 44÷2

ዋቢ መጻሕፍት



- የትንቢተ ሕዝቅኤል መቅድም
- መቅረዝ ዘተዋሕዶ
- መጽሐፈ ስንክሳር
- A Patristic Commentary on Ezekiel by Fr. Tadros Malaty

ስብሐት

ለእግዚአብሔር